የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARITGAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፲፱፻፺፯

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

11th Year No. 45
ADDIS ABABA- 15th July, 2005

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፯/፲፱፻፺፯ ዓ.ም

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት አዋጅ...ገጽ ፫ሺ፩፻፵፭

CONTENTS

Proclamation No. 457/2005

Raw Hide and Skin Marketing System Proclamation....Page 3145

## አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፯/፲፱፻፺፯

## ስለጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት የወጣ
## አ ዋ ጅ

የጥሬ ቆዳና ሌጦ አዘገጃጀትና ግብይት ሥርዓት በጥራ ደረጃ ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና የምርቱ አሰባሰብ፣ አዘገጃጀት፣ አከማቻቸትና አጓጓዝ ሂደት ተሻሽሎ ከንዑስ ዘርፉ ሊገኝ የሚገባው ጥቅም እንዲገኝ ማድረግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፬፻፶፯/፲፱፻፺፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### ፪. ት ር ጓ ሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩/ "የግብይት ሥርዓት" ማለት ጥሬ ቆዳንና ሌጦን የመሰብሰብ፣ የማዘጋጀት፣ የማጓጓዝና የመሸጥ ሂደት ነው፣

## PROCLAMATION NO. 457/2005

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR RAW HIDE AND SKIN MARKETING SYSTEM

**WHEREAS**, it has been found necessary, that the processing and marketing system of raw hide and skin should be based upon quality, and that the collection, processing, warehousing and transportation process of the product should be improved with a view to obtaining the benefit that could accrue from the sub sector;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Raw Hide and Skin Marketing System Proclamation No.457/2005."

### 2. Definition

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ "marketing system" means the collection, processing, transporting and selling process of raw hide and skin;

ያንዱ ዋጋ 2.80
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፪ "ጥሬ ቆዳ" ማለት ከበሬ፣ ከወይፈን፣ ከላም፣ ከጊደር ወይም ከግመል የሚገኝ ትኩስ ወይም በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ቆዳ ሲሆን ሚኒስቴሩ ጥሬ ቆዳ ብሎ የሚሰይማቸውንም ያጠቃልላል፣

፫/ "ጥሬ ሌጦ" ማለት ከበግ፣ ከፍየል፣ ከጥጃ ከአዞ ወይም ከዓሣ የሚገኝ ትኩስ ወይም በአየር የደረቀ ወይም በጨው የተዘጋጀ ሌጦ ሲሆን ሚኒስቴሩ ጥሬ ሌጦ ብሎ የሚሰይማቸውንም ያጠቃልላል፣

፬/ "ትኩስ ቆዳ ወይም ሌጦ" ማለት በጨው ያልታጀለ ወይም በአየር ያልደረቀ እርጥብ ቆዳ ወይም ሌጦ ነው፣

፭/ "የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት" ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለመሰብሰብ፣ ለማዘጋጀትና ለማጓጓዝ የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ነው፣

፮/ "የግብይት ተሳታፊዎች" ማለት በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰብሳቢዎች፣ አቅራቢዎች፣ ቄራዎችና ፋብሪካዎች ናቸው፣

፯/ "ማጓጓዣ" ማለት ጥሬ ቆዳና ሌጦን ለማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጥ ተሽከርካሪ ሲሆን የጭነት እንስሳትንም ያጠቃልላል፣

፰/ "ሚኒስቴር" ማለት የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ነው፣

፱/ "አግባብ ያለው ባለሥልጣን" ማለት የኤክስፖርት ግብይት ሥርዓትን በሚመለከት ሚኒስቴሩ ሲሆን የአገር ውስጥ ግብይት ሥርዓትን በሚመለከት የግብርናና የገጠር ልማትን የሚከታተል የክልል አካል ነው፣

፲/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው::

## ፫. ተፈጻሚነት

ይህ አዋጅ በጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## ፬. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

፩/ ማንኛውም ሰው የጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ ፍቃድ ከማውጣቱ በፊት አግባብ ካለው ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይኖርበታል::

2/ "raw hide" means any fresh, air-dried or salted hide obtained from bull, ox, cow, heifer or camel and includes any other hide designated as such by the Ministry;

3/ "raw skin " means any fresh, air-dried or salted skin obtained from sheep, goat, crocodile, calf or fish and includes any other skin designated as such by the Ministry;

4/ "fresh hide or skin" means unsalted or not air-dried hide or skin;

5/ "certificate of competence" means a certificate issued to certify eligibility for collecting, preserving, storing and transporting raw hide and skin;

6/ "marketing participants" means collectors, suppliers, abattoirs and factories that are engaged in the trading of raw hides and skins;

7/ "means of transportation" mans a vehicle which provides service to transport raw hides and skins and includes pack animals;

8/ "Ministry" means, the Ministry of Agricul- ture and Rural Development;

9/ "competent authority" means the Ministry, as regards to the export marketing system, and a regional body in charge of following up agricultural and rural development activities, as regard to the domestic marketing system;

10/ "person" means a natural or a juridical person.

## 3. Scope of Application

This Proclamation shall be applicable to all raw hide and skin marketing participants.

## 4. Certificate of Competence

1/ Prior to obtaining raw hide and skin trading license, it is compulsory to get certificate of competence from the competent authority;

፪/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘትም ሆነ ለማሳደስ መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

**፭. ጥሬ ቆዳና ሌጦ ስለማዘጋጀትና ስለማጓጓዝ**

፩/ ማንኛውም ቆዳና ሌጦን የሚያዘጋጅ ሰው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተሟላ የቆዳና ሌጦ ማደራጃ ድርጅት ሊኖረው ይገባል፣

፪/ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ከማደራጃ ድርጅት ወደ ሌላ አካባቢ መጓጓዝ የሚችለው ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሲሆን ጭነቱ አግባብ ባለው አካል በሚመደብ ተቆጣጣሪ በፕሎምፕ መታሸግና በተቆጣጣሪው የተፈረመ የመሸኛ ወረቀት እንዲኖረው ይደረጋል፣

፫/ ማንኛውም ጥሬ ቆዳና ሌጦ የሚያጓጉዝ ሰው ለጭነቱ የሚሰጠውን የመሸኛ ወረቀት መያዝና አግባብ ባለው ባለሥልጣን በተመደበ ተቆጣጣሪ ሲጠየቅም ማሳየት አለበት።

**፮. የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት**

የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት በማንኛውም እርከን የኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን በሚያወጣው የጥራት ደረጃ፣ እና

፩/ ጥሬ ሌጦ ሲሆን በስፋት፣

፪/ ጥሬ ቆዳ ሲሆን በክብደት፣

ላይ የተመሠረተ ይሆናል።

**፯. ክልከላ**

፩/ ማንኛውም ሰው የንግድ ፈቃድ ሳይኖረው በጥሬ ቆዳና ሌጦ ንግድ መሰማራት አይችልም፣

፪/ ማንኛውም ሰው ጥሬ ቆዳና ሌጦ ወደ አልተፈቀደለት አካባቢ ማጓጓዝና መሸጥ አይችልም።

**፰. ስለግብይት መረጃ**

ማንኛውም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊ የየራሱን፣

፩/ የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግዥ መጠንና ዋጋ፣

2/ The criteria and pre-conditions required for issuance and renewal of certificate of competence shall be determined by the directives to be issued by the Ministry.

**5. Processing and Transportation of Raw Hides and Skins**

1/ A person who processes raw hides and skins shall have appropriate facilities built as per the directives issued by the Ministry;

2/ Raw hides and skins could be transported from the processing facility to any other place in accordance with the directives issued by the Ministry. The consignment shall be sealed in plump by an inspector assigned by the competent authority and that it shall be accompanied by a certificate signed by the inspector;

3/ A person who transports raw hide and skin shall keep with him the certificate of consignment and shall present it when requested by any inspector assigned by the competent authority.

**6. Raw Hide and Skin Marketing**

Raw hide and skin marketing shall be carried out at any level, on the basis of the quality standards issued by the Ethiopian Quality and Standards Authority, and on the basis of:

1/ width where it is raw skins;

2/ weight where it is raw hide.

**7. Prohibition**

1/ No person shall engage in raw hide and skin trade without obtaining a trade license;

2/ No person shall transport and sell raw hide and skin to areas not authorized.

**8. Marketing Information**

Any raw hide and skin marketing participant shall:

1/ keep record of own daily purchased quantity and price of raw hide and skin;

፪/ የየዕለቱን የጥሬ ቆዳና ሌጦ ሽያጭ መጠንና የተቀባይ ዝርዝር፣ እና

፫/ በየዕለቱ የገዛውን የጥሬ ቆዳና ሌጦ የጥራት ደረጃ መረጃዎችን፣

መዝግቦ መያዝና አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሲጠየቅ መስጠት አለበት።

## ፱. ስለቁጥጥርና አስተዳደራዊ እርምጃዎች

፩/ አግባብ ባለው አካል የተመደበ ተቆጣጣሪ መታወቂያውን በማሳየት የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ መተግበራቸውን ይቆጣጠራል፣

፪/ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ግብይት ተሳታፊ ይህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን ካላከበረ የንግድ ፍቃዱ ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፣

፫/ በአገሪቱ ልዩ ልዩ አዋጆች አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፈቃድ በሌለው ሰው ተከማችቶ ወይም ሲጓጓዝ የተገኘ ጥሬ ቆዳና ሌጦ እንደኮንትሮባንድ እቃ ተቆጥሮ ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል፣

፬/ ቆዳና ሌጦ ፈቃድ በሌለው ሰው መከማቸቱን ወይም መጓጓዙን ለጠቆመና ላስያዘ ሰው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ኮሚሽን እንዲከፈለው ሊደረግ ይችላል።

## ፲. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የቆዳና ሌጦ ኤክስፖርት ግብይት ሥርዓትን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና መመሪያዎችን ሚኒስቴሩ ሊያወጡ ይችላሉ፣

፪/ የቆዳና ሌጦ የአገር ውስጥ ግብይት ሥርዓትን በሚመለከት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችንና መመሪያዎችን ክልሎች ሊያወጡ ይችላሉ።



2/ record and keep of own daily sales quantity and buyers of raw hide and skin;

3/ maintain quality information of the daily purchased raw hide and skin;

and shall furnish same when requested by the competent authority.

## 9. Inspection and Administrative Measures

1/ An inspector assigned by the competent authority shall, upon showing his identification card, make inspection to ensure the proper implementation of the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder.

2/ The trade license of a raw hide and skin marketing participant may be suspended or cancelled where he fails to comply with the provisions of this Proclamation and regulations and directives issued hereunder.

3/ Without prejudice to administrative measure that may be taken by the appropriate Authority, if raw hides and skins found stored or transported by a person having no license may be considered as contraband goods and appropriate punishment measure will be taken.

4/ A person who provides information leading to the seizure of hides and skins stored or transported by unlicensed trader may be, paid a commission by the competent authority.

## 10. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers and the Ministry may issue regulations and directives, respectively, necessary for the proper implementation of this Proclamation with respect to hides and skin export marketing system.

2/ Regional states may issue regulations and directives necessary for the proper implementation of this Proclamation with respect to hide and skin domestic marketing system.

## ፲፩. የተሻሩ ህጎች

፩/ የቆዳና ሌጦ ደንብ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፷፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፣

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

## ፲፪. አዋጁ የሚፀናበት

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፰ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## 11. Repealed Laws

1/ The Raw Hide and Skins Regulation No. 25/1975 is hereby repealed.

2/ No law, regulation, directive or practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 12. Effective Date

This Proclamation shall enter into force on this 15th date of July, 2005

**Done at Addis Ababa, this 15th day of July, 2005.**

GIRMA WOLDEGIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA